በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

የጡረታ ፈንድ አሰባሰብ ፣ አያያዝ እና አጠቃቀምን

በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት

/FOLLOW UP AUDIT/ ሪፖርት

ህዳር 2009 ዓ.ም

ማውጫ

የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (ድርሞ)..1
ክፍል አንድ..3
መግቢያ...3
የኤጀንሲው አመሰራረት 3
የክትትል ኦዲቱ ዓላማ...4
የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ 5
የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች...6
ክፍል ሁለት 7
በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች...7
የጡረታ መዋጮ ሰብሳቢዎችና የጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ስለመደረጉ፡-..7
የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ በወቅቱ ገቢ ስለመደረጉ እና ከየትኞቹስ መ/ቤቶች እንደተሰበሰበ ስለመታወቁ ፡- 8
ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ያለባቸው መ/ቤቶች ላይ በኤጀንሲው ምርመራ ስለመደረጉ ፡-..11
ሊቀነስ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በመቀነስ ለጡረታ ፈንዱ በወቅቱ ገቢ ያላደረገ መ/ቤት ላይ እርምጃ ስለመወሰዱ፡-..11
ለጡረታ ፈንዱ የሚያገለግለውን የሂሳብ አሰራር ማንዋል (መመሪያ) ወቅታዊ / ዘመናዊ/ እንዲሆን ስለመደረጉ፡- 14
የጡረታ ፈንድ አቋም የሚያሳይ የሂሳብ ትንታኔ (የሂሳብ መግለጫ) በየዓመቱ መዘጋጀቱን እና ኦዲት መደረጉን በተመለከተ፡-...15
በአሰሪ መ/ቤቶች ስም የተከፈተው የገቢ ሂሳብ ሌጀር ወቅታዊ ስለመሆኑ፡-.............16
ለሪል ስቴት ወጪ ተደርጎ የተከፈለው ሂሳብ የተመለሰ ስለመሆኑ እና ቦታው ለሚመለከተው የመንግስት አካል መረከቡን በተመለከተ፡-..16
የገንዘብ መክፈያ ፔይሮል ላይ በጣት አሻራ ብቻ በተደረገ ምልክት ሂሳብ ስለመወራረዱ፡-..18
የጡረታ ፈንዱ የማስረጃ አያያዝና አጠባበቅ አንድ ወጥ እና አስተማማኝ መሆኑን በተመለከተ ፡-...19

የቋሚ የመንግስት ሠራተኞች የምዝገባ ማስረጃ ተሟልቶ እንዲቀርብ እና የማህበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር በወቅቱ እንዲሰጥ ስለመደረጉ 21
105. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤ 21
ለጡረታ መዋጮ ሰብሳቢዎች ፣ አበል ከፋዮች እና አሰሪ መ/ቤቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ   መድረክ ስለመዘጋጀቱ ፡- 22
ክፍል ሦስት 24
የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion) 24
3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው 24
3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው 25
ክፍል አራት 27
የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation) 27

የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (ድርሞ)

(Executive summary)

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2004/2005 ዓ.ም በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የጡረታ ፈንድ አሰባሰብ፣ አያያዝ እና አጠቃቀምን በተመለከተ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን ፤ እንዲሁም ኤጀንሲው የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ በደብዳቤ ቁጥር ሐጣት.1/16/94/05 መጋቢት 12 ቀን 2005 ዓ.ም. ለመ/ቤታችን ባቀረበው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት ያከናወነ መሆኑን የክትትል ኦዲት በማድረግ የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም መገምገም ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በማየትና በማጣራት ችግሮች እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ መስጠት ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት በክትትል ኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው :-

- በራሳቸው በጀት የሚተዳደሩ መ/ቤቶች የጡረታ መዋጮ የሚሰበሰበው በገቢዎች ባለስልጣን ሲሆን በገቢዎች ባለስልጣን ላይ በራሳቸው በጀት ከሚተዳደሩ መ/ቤቶች የጡረታ መዋጮ በትክክል ስልመሰብሰቡ ቁጥጥር እና ክትትል የማይደረግ መሆኑን፣
- ከሠራተኞች የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ በወቅቱ ገቢ የማይደረግበት መሆኑን ፣ በገቢዎች ባለስልጣን የሚሰበሰበው በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ መ/ቤቶች የጡረታ መዋጮ ከየትኞቹ መ/ቤቶች እንደተሰበሰበ በአብዛኛው የማይታወቁ መሆኑን፣
- ከሠራተኞች ሊቀነስ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በመቀነስ በወቅቱ ለፈንዱ ገቢ ያላደረገ የመንግስት መ/ቤቶች ላይ ወለድ እና አምስት ፐርሰንት ቅጣት እንዲከፍሉ የማይደረግ መሆኑን፣
- ለጡረታ ፈንዱ የሚያገለግል በ1992 ዓ.ም የወጣ መመሪያ ወቅታዊ / ዘመናዊ / ለማድረግ የተሰራ ስራ የሌለ መሆኑን፣
- የጡረታ ፈንድ አቋም የሚያሳይ የሂሳብ ትንታኔ (የሂሳብ መግለጫ) በየዓመቱ እየተዘጋጀ እና ኦዲት እየተደረገ አለመሆኑን፣

- አንዳንድ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች የጡረታ መዋጮውን በአሰሪ መ/ቤቶች ሥም በተከፈተ ሌጀር መዝግበው ያልያዙ መሆኑን ፣
- ኤጀንሲው ለተለያዩ አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉ ህንጻዎች ለመገንባት ካወጣው 5,301,741.17 ብር ውስጥ የአሰላ እና የደብረማርቆስ ገቢ ያልተደረገ መሆኑን ፣
- መፈረም ከሚችሉ የጡረታ ባለመብቶች መካከል አብዛኛው በጣት አሻራ እንዲፈርሙ የሚደረግ መሆኑን፣
- የመንግሥት ሠራተኞችን ምዝገባ የሚመለከቱ ማስረጃዎችን በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ / ፔንሽን አድሚን ሶፍትዌር / ያላቸው ሪጅን ፅ/ቤቶች በተሟላ ሁኔታ ያልተመዘገበ መሆኑን ፣ በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ / ፔንሽን አድሚን ሶፍትዌር / የሌላቸው ሪጅን እና ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች መኖራቸው፣
- የጡረታ ፈንዱን የሚመለከቱ ማስረጃዎች ደግሞ በማንዋል የተያዙ ሲሆን ፣ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ የሌለ መሆኑን ፣
- በአንዳንድ የመንግስት መ/ቤቶች የቋሚ የመንግስት ሠራተኞች የምዝገባ ማስረጃ ተሟልቶ እንዲቀርብ እና የማህበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር በወቅቱ እንዲሰጥ የማይደረግ መሆኑ፣
- ለጡረታ አበል ከፋይ እና ሰብሳቢ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ተዘጋጅቶ የማይሰጣቸው መሆኑን፣

  እስካሁን መኖሩ ታውቋል፡፡

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. በህገ-መንግሥቱ የተገለጸውን የዜጎችን ማኅበራዊ ዋስትና የማግኘት መብት ለማረጋገጥ፤ ድህነትን ለመቀነስና የሠራተኞችን የሥራ ውጤታማነት ለማሳደግ ከሚቀየሱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መካከል አንዱ የማኅበራዊ ዋስትና ማስፋፊያ ነው፡፡ የአገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንዲሟሉለት ከሚያስፈልጉት የአገልግሎት መብቶች መካከል የማኅበራዊ ዋስትና የሚጠቀስ ነው ፡፡ የዜጎችን የማኅበራዊ ደህንነትና ጥቅሞችን ለመጠበቅ የማኅበራዊ ዋስትና አገልግሎት ሽፋን በስፋት እንዲዳረስ ለማድረግ የማኅበራዊ ዋስትና ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡

2. የጡረታ መዋጮ ገቢን ወቅቱን ጠብቆ በአግባቡ አለመሰብሰብ፤ የጡረታ አበል ክፍያ ባለመብቶች ብዛት እየጨመረ መምጣትን ተከትሎ የፈንዱን አስተማማኝነት ስጋት ላይ ስለሚጥል የጡረተኞች የገቢ ምንጭ መቋረጥን ሊያስከትል ይችላል፡፡ ስለሆነም የዜጎችን የማህበራዊ ዋስትና ከማረጋገጥ አንጻር የመንግሥት ሠራተኞችን ጡረታ ለመደንገግ አዋጅ ቁጥር 714/2003 እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

3. ኦዲቱ እንዲከናወን ያስፈለገበት ምክንያት የተመረጠው የኦዲት አካባቢ የህግ አውጭውንና የህዝቡን ትኩረት የሚስብና ከፍተኛ ሥጋት ያለበት በመሆኑ፣ በአገሪቱ የጡረታ መዋጮ በወቅቱ በተሟላ ሁኔታ መሰብሰቡና የተሰበሰበው የጡረታ ፈንድ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉ ቢረጋገጥ ለወደፊቱ የጡረታ ፈንዱ አስተማማኝነት እንዲኖረው ስለሚረዳ ነው፡፡

የኤጀንሲው አመሰራረት

4. በህመም ወይም በዕድሜ መግፋት ምክንያት ሥራ ለመሥራት የማይችሉ፣ በጦር ሠራዊትነት አገልግለው ማደሪያና ጧሪ ልጅ የሌላቸው፣ በልዩ ልዩ ምክንያት ርስታቸውን አጥተው ጧሪ ልጅ የሌላቸው፣ በቤተ መንግሥት ሲያገለግሉ ኖረው ጧሪ ያጡ አረጋውያን አሰባስቦ የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎት ለመስጠት ታስቦ የዳግማዊ ምኒሊክ መታሰቢያ ቤት የሚል በ1925 ዓ.ም በሀገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በመንግሥት ደረጃ ተቋቋመ፡፡

5. ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሁፍ የወጣ የጡረታ ህግ ነበር ለማለት የሚያስደፍር ደንብ ቁጥር 3502/1926 የጡረተኞች ማስተዳደሪያ ጽ/ቤት በሚል ስያሜ ተቋቁሞ የተጧሪዎችን ጉዳይ በመከታተል አገልግሎት እንዲሰጥ ተደረገ፡፡

6. በመቀጠልም ለዘመናዊ የሀገራችን ማህበራዊ ዋስትና የመሰረት ድንጋይ የጣለው የጡረታ ድንጋጌ ቁጥር 46/1953 የወጣ ቢሆንም፣ ብዙም ሳይቆይ በንጉሡ ትእዛዝ ለፓርላማ ቀርቦ እንዲመከርበት ከተደረገ በኋላ እንዳንድ ማሻሻያዎች ተደርገውበት የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 209/55 በነጋሪት ጋዜጣ እንዲወጣ ተደረገ፡፡

7. መ/ቤቱ በተለያዩ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ሲመራ ከቆየ በኋላ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ሚያዚያ 26/1958 በተጻፈ ደብዳቤ ከመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መ/ቤት ጋር ተጣምረው የሚኒስትር ማዕረግ ባለው በአንድ የበላይ ኮሚሽነር እንዲመሩ ተደረገ፡፡ የመ/ቤቱም ስያሜ የመንግሥት አገልግሎት ጡረታ ጉባዔ ተባለ፡፡ ቀጥሎም አዋጅ ቁጥር 209/55 ለማሻሻል አዋጅ ቁጥር 5/67፣ ወታደሩን በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 6/67፣ በግል ይዞታ ስር የነበሩ ሠራተኞች በጡረታ ህግ እንዲሸፈኑ ያደረገው አዋጅ ቁጥር 49/67 እንዲወጣ ተደረገ፡፡ በመቀጠልም በአዋጅ ቁጥር 38/88 ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በመሆን ማኅበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በሚል ስያሜ በፌዴራል መ/ቤትነት ተቋቁሞ በቦርድ እንዲመራ ተደረገ፡፡

8. የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ተግባሩን በብቃት ለማከናወን በሚችልበት ሁኔታ እንደገና ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ኤጀንሲውን እንደገና ለማቋቋም አዋጅ ቁጥር 495/98 ወጥቷል፡፡ በመጨረሻም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 203/2003 የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እየተባለ የሚጠራ የህግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት ሆኖ ቁጥራቸው እንደ አስፈላጊነቱ በሚወሰን በመንግሥት የሚሰየሙ ሰብሳቢና አባላት ባሉት ቦርድ እንዲመራ ተደርጎ ተቋቋመ፡፡

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ

9. የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2004/2005 ዓ.ም በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የጡረታ ፈንድ አሰባሰብ፣ አያያዝ እና አጠቃቀምን በተመለከተ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን ፤ እንዲሁም

ኤጀንሲው የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ በደብዳቤ ቁጥር ሐጣት.1/16/94/05 መጋቢት 12 ቀን 2005 ዓ.ም. ለመ/ቤታችን ባቀረበው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት ያከናወነ መሆኑን የክትትል ኦዲት በማድረግ የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም መገምገም ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በማየትና በማጣራት ችግሮች እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ መስጠት ነው፡፡

የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

10. የክትትል ኦዲቱ የሸፈነው ከ2006-2008 ዓ.ም ያሉትን የሶስት በጀት ዓመታት የሥራ ክንውኖችን እንቅስቃሴ መሰረት ባደረገ በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የጡረታ ፈንድ አሰባሰብ፣ አያያዝ እና አጠቃቀምን ላይ በተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ለተገኙ ግኝቶች/ግድፈቶች/ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦችን እና ኤጀንሲው እነዚህን የኦዲት ግኝቶች የሚፈታበት የኦዲት ግኝት ማሻሻያ ሃሳቦች የሚተገበሩበትን የማሻሻያ እርምጃ የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ባቀረበው መሰረት የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች በተዘጋጀው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት መተግበራቸውን እና ችግሮቹ መቀረፋቸውን ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲቱ እስከተከናወነበት እስከ 2009 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ በኤጀንሲው የተከናወኑ ስራዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

11. የክትትል ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ዋና መ/ቤት እና በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመረጠው ከታዩ ሪጅን ፅ/ቤቶች ፣ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ፣ የጡረታ አበል ሰብሳቢ ተቋማት ፣ የጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት እና አሰሪ መ/ቤቶች መካከል መሀል ሪጅን ፅ/ቤት ፣ አዲስ አበባ ሪጅን ፅ/ቤት ፣ ደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ፣ አርባምንጭ ቅ/ፅ/ቤት ፣ ሶዶ ቅ/ፅ/ቤት ፣ ሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤተ ፣ ደቡብ ክልል ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት ፣ ደቡብ ክልል ገቢዎች ባለስልጣን ፣ ደቡብ ሪጅን ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ፣ አርባምንጭ ከተማ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት ቢሮ ፣ አርባምንጭ ከተማ ገቢዎች ባለስልጣን ፣ ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ አርባምንጭ ቅርንጫፍ ፣ አርባምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ፣ የግል ድርጅቶች ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ አርባምንጭ ቅ/ፅ/ቤት ፣ ወላይታ ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት ፣ ወላይታ ዞን ገቢዎች ባለስልጣን ፣ ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ወላይታ ቅርንጫፍ ፣ ሆሳዕና ከተማ

ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት እና ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ሆሳዕና ቅርንጫፍ ፣ መ/ቤቶች በመገኘት ለሚመለከታቸው ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ለክክትል ኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን በመከለስና በመተንተን የተካሄደ ነው፡፡

የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

12. የክትትል ኦዲቱን ለማከናወን እንደመመዘኛ መስፈርት የተመረጡት በኦዲቱ ወቅት የነበሩ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ናቸው፡፡

ክፍል ሁለት

በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች

የጡረታ መዋጮ ሰብሳቢዎችና የጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ስለመደረጉ፡-

13. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

14. አዋጅ ቁጥር 714/2003 ከመውጣቱ በፊት አሰሪ መ/ቤቶች ከሰራተኞቻቸው ደመወዝ እየቆረጡ የሰበሰቡትን የጡረታ መዋጮ ገቢ ማድረጋቸውን ለመከታተል የተዘረጋ ስርአት አለመኖሩን፣ አዋጅ ቁጥር 714/2003 ከወጣ በኋላም በተለይ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከሰራተኞቻቸው የሰበሰቡትን የጡረታ መዋጮ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ እንዲችሉ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጋር ውል የተዋዋሉ ቢሆንም፣ መሰብሰብ ያለበትን የጡረታ መዋጮ በውሉ መሰረት ለመሰብሰብ የሚያስችል ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

15. የጡረታ መዋጮ ሰብሳቢዎች እና የጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ከኤጀንሲው ጋር ግልፅ የሆነ የሥራ ግንኙነት፣ ኃላፊነት እና ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚያስችል ሥርዓት እንዲኖር በማድረግ ያልተሰበሰበ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ቢኖርም የውዝፉ መጠንና ያልከፈሉት እነማን መሆናቸው ሊታወቅ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

16. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሐጣት.1/16/94/05 በቀን 12/07/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር መካከል የጡረታ መዋጮ ሰብሳቢዎች እና የጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ላይ ስለሚደረግ ክትትል እና ቁጥጥር በመርሃ -ግብሩ ላይ አላካተተም፡፡

17. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

18. በመሀል ሪጅን ፅ/ቤት ፣ በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ፣ በአርባምንጭ ቅ/ፅ/ቤት ፣ በሶዶ ቅ/ፅ/ቤት እና በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት በጡረታ መዋጮ ሰብሳቢዎች ላይ በዓመት አንድ ጊዜ አሰሪ መ/ቤቶች ላይ ምርመራ በማድረግ ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግ ሲሆን በጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ላይ ደግሞ ለጡረታ ባለመብቶች ክፍያ ከተፈፀመ በኋል በክፍያ ፔሮሉ መሰረት ትክክለኛነቱን በማረጋገጥና መተማመኛ በመፈራረም ክትትል እና

ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ፣ በራሳቸው በጀት የሚተዳደሩ መ/ቤቶች የጡረታ መዋጮ የሚሰበሰበው በገቢዎች ባለስልጣን ሲሆን በገቢዎች ባለስልጣን ላይ ግን ቁጥጥር እና ክትትል የማይደረግ መሆኑን ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

19. በደ/ብ/ብ/ክ/መ/ ገቢዎች ባለስልጣን የጡረታ አሰባሰብ ስርዓቱ ተግባራዊ ስለመደረጉ በመንግስት ማህበራዊ ኤጀንሲ ቁጥጥር እና ክትትል የማይደረግ መሆኑን ከደቡብ ክልል ገቢዎች ባለስልጣን የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

20. በደቡብ ሪጅን ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ክትትል እና ቁጥጥር ላይ ክፍተት ያለ መሆኑን ከደቡብ ሪጅን ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ የሥራ ሃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል ፡፡

21. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ በገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ላይ በኤጀንሲው መ/ቤት የውስጥ ቁጥጥር / ኦዲት ዳይሬክቶሬት ከ1/11/2006-30/10/2007 ዓ.ም ያለውን አፈፃፀም ዝርዝር የኦዲት ግምገማ ተካሂዶ ሪፖርት መቅረቡን፣ በተጨማሪም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለስልጣን እና በመሐል ሪጅን በገቢዎች ባለስልጣን መ/ቤት ከኤጀንሲው ጋር በገባው ውል መሰረት ስለመፈፀሙ ምርመራ መካሄዱን ገልፀዋል፡፡

22. ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የኤጀንሲው ሪጅን ፅ/ቤቶች፣ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች እንዲሁም የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤቶች ኤጀንሲው ክትትል እና ቁጥጥር እንደማያደርግ ገልፀዋል፡፡

የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ በወቅቱ ገቢ ስለመደረጉ እና ከየትኞቹስ መ/ቤቶች እንደተሰበሰበ ስለመታወቁ ፡-

23. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

24. ኤጀንሲው ከአዋጅ ቁ.714/2003 በፊት ያለውን ውዝፍ የጡረታ መዋጮ በእያንዳንዱ የመንግሥት መ/ቤት ላይ ክትትል አድርጎ አለመሰብሰቡን፣

25. ከ14/07/2004-30/09/2004 ባለው ጊዜ ውስጥ በቀረበው የሂሳብ የምርመራ ሪፖርት መሰረት ከተመረመሩት መ/ቤቶች መካከል ለምሳሌ ከመሀል ሪጅን ጽ/ቤት፣ ከአ.አ ሪጅን ጽ/ቤት እና ከደቡብ ሪጅን ጽ/ቤት፣ ብር 182,039,915 በአሰሪ መ/ቤቶች ላይ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ መኖሩ ተረጋግጦ መተማመኛ የተሰጠ ቢሆንም ገንዘቡ ገቢ የተደረገበት

ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑን ፣ በሀድያ ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት ከሰኔ 2003 ጀምሮ እስከ ነሀሴ 2004 ድረስ እንዲሁም ከሀድያ ማዘጋጃ ቤት ሠራተኞች ደመወዝ ተቀንሶ የቀረ የጡረታ መዋጮ ወደ ኤጀንሲው ገቢ ያለመደረጉን፣

26. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት መ/ቤቶች ውስጥ ከሠራተኛው ደመወዝ ቀንሰው ወደ ጡረታ ፈንዱ ሳያስገቡ የቀሩ መ/ቤቶች እንደሚገኙና የነዚህም ሁኔታ ሲጣራ፣ የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤት እንደሌሎች ሴክተር መ/ቤቶች እየተቀነሰ እንዲቀር የማይደረግ ስለሆነ በአዲሱ አዋጅ መሰረት ከሰኔ/2003 ጀምሮ የጡረታ መዋጮ ያልከፈለ መሆኑን፤

27. እንዲሁም የጡረታ መዋጮው ከየትኛው መ/ቤት፣ ዞን፣ ወረዳ እንደተሰበሰበ ባለመታወቁ በዚህም የተነሳ የትኛው መ/ቤት የጡረታ መዋጮውን በወቅቱ ገቢ ማድረጉንና አለማድረጉን ለመለየት ያልተቻለ መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

28. የሚፈለግባቸውን ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ገቢ ያላደረጉ የክልል መንግሥታትም ሆነ የፌዴራል መንግሥት ከሚሰጣቸው የድጎማ በጀት ላይ ተቀንሶ ለኤጀንሲው ገቢ ሊደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

29. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሐጣት.1/16/94/05 በቀን 12/07/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር እስከ ታህሳስ 30/2006 ዓ.ም ያልተሰበሰቡ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ የውዝፍ መጠን እና ያልተከፈሉ እነማን መሆናቸውን በመለየት መስራትና በቀጣይ በተዘረጋው ስርዓት እና በውሉ መሰረት የመከታተል እና የመፈፀም ስራ እንደሚሰራ ገልጿል፡፡

30. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

31. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ መ/ቤቶች መካከል በመሀል ሪጅን ፅ/ቤት ከሠራተኞች የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ በወቅቱ ገቢ የማይደረግበት ጊዜ መኖሩን፣ በገቢዎች ባለስልጣን የሚሰበሰበው በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ መ/ቤቶች ከሰራተኞች የሚሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ ብሩን ባንክ በሚያስገባው በግለሰብ ስም ወይም በዝውውር ስለሚያስገቡ ከየትኞቹ መ/ቤቶች እንደተሰበሰበ በአብዛኛው የማይታወቁ መሆኑን፣ አንዳንድ ራቅ ያሉ ወረዳዎች ላይ የጡረታ መዋጮ በወቅቱ የማይሰበሰብበት ሁኔታ መኖሩን ፣ ወረዳዎች ላይ ሀላፊ ሲቀያየር ስለጡረታ መዋጮ ግንዛቤ ስለማይኖራቸው እና የግንዛቤ እጥረት ስላለባቸው

የጡረታ መዋጮ በወቅቱ እንደማይሰበሰብ ፣ የጡረታ መዋጮውን ለበጀት የሚጠቀሙበት መ/ቤቶችም መኖራቸውን፣

32. በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ከመንግስት ሠራተኞች የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮን በተመለከተ በደቡብ ክልል ፋይናንስ ቢሮ (በባለበጀት መ/ቤቶች) የሚሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ በወቅቱ ገቢ የሚደረግ መሆኑን፣ ከየትኞቹ መ/ቤቶችም እንደተሰበሰበ የሚታወቅ መሆኑን፣ ነገር ግን በገቢዎች ባለስልጣን የሚሰበሰበው (በራሳቸው በጀት የሚተዳደሩ መ/ቤቶች) የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ የማይደረግ መሆኑን፣ ከየትኞቹ መ/ቤቶች እንደተሰበሰበ የማይታወቅ መሆኑን፣

33. በአርባምንጭ ቅ/ፅ/ቤት ከመንግስት መ/ቤቶች የተሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ የማያደርጉ መ/ቤቶች መኖራቸውን ፣

34. በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት በገቢዎች በኩል የሚሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ደቡብ ሪጅን ሀዋሳ ስለሚገባ ምንም መረጃ የሌላቸው መሆኑን ፣ ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ እና ከባንክ ስቴትመንት ለማወቅ መቻሉን፡፡

35. እንዲሁም በአርባምንጭ ከተማ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት ቢሮ እና ከሆሳዕና ከተማ አስተዳደር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ዋና ፅ/ቤት ከመንግስት ሠራተኞች የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ገቢ የማይደረግ መሆኑን የስራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

36. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የሪጅን ፅ/ቤቶች እና ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ውስጥ ከሚገኙ አሰሪ መ/ቤቶች መካከል ውዝፍ የጡረታ መዋጮ በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

37. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ በገቢዎች በኩል ክፍያ የሚፈፅሙ መ/ቤቶች መዋጮውን በወቅቱ ከመክፈል አኳያ ውስንነቶች ያለባቸው መሆኑን፣ ሪጅንና ቅ/ፅ/ቤቶች በዓመት አንድ ጊዜ በአመት አንድ ጊዜ በሚያደርጉ መዋጮ ገቢ ምርመራ ውዝፍ ዕዳ ሲገኝባቸው ከባንክ አካውንታቸው የማስቆረጥ የሚሰራ ሲሆን አርባምንጭ እና ሆሳዕና ከተማ መስተዳድሮች ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ገቢ መኖሩ ተረጋግጦ እንዲያስገቡ በተደጋጋሚ በደብዳቤ የተገለፀላቸው ቢሆንም የበጀት እጥረት አለብን በማለት የዘገዩ በመሆናቸው በጡረታ አዋጁ መሰረት ቀጣዩ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የመጨረሻ እርምጃ እንዲሰጣቸው መደረጉን ገልፀዋል፡፡

ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ያለባቸው መ/ቤቶች ላይ በኤጀንሲው ምርመራ ስለመደረጉ ፡-

38. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

39. መሰብሰብ የሚገባው የጡረታ መዋጮ መኖሩ እንጂ ውዝፍ መዋጮ ያለባቸው መ/ቤቶች ተለይተው የማይታወቁ ከመሆኑም በላይ ያልተሰበሰበውን ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ትክክለኛውን መጠን ለይቶ ለማወቅ የማይቻል መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

40. በፌዴራልም ሆነ በክልል የጡረታ መዋጮ ከፋይ በሆኑ አሰሪ መ/ቤቶች መሰብሰብ የሚገባው ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ለመሰብሰቡ በኤጄንሲው ምርመራ ሊካሄድ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

41. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሐጣት.1/16/94/05 በቀን 12/07/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ እስከ ሰኔ 30/2006 ዓ.ም ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ያለባቸውን በኤጀንሲው ምርመራ ያልተካሄደባቸው ላይ ምርመራ በማከናወን ውዝፍ ያለባቸውን የመለየት ስራ እንደሚሰራ ገልጿል፡፡

42. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

43. በአዲስ አበባ ሪጅን ፅ/ቤት፣ በመሀል ሪጅን ፅ/ቤት፣ በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት፣ በአርባምንጭ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ፣ በሶዶ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት እና በሆሳዕና ቅርንጫፍ ፅ/ቤት የጡረታ መዋጮ ከፋይ በሆኑ አሰሪ መ/ቤቶች መሰብሰብ የሚገባው ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ለመሰብሰቡ በዓመት አንድ ጊዜ ምርመራ የሚደረግ ሲሆን በኤጀንሲው ዋና መ/ቤት በ 2006 ዓ.ም ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ለመሰብሰብ ምርመራ ያልተደረገ መሆኑን ለኦዲት ቡድኑ ከቀረቡት የምርመራ ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

ሊቀነስ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በመቀነስ ለጡረታ ፈንዱ በወቅቱ ገቢ ያላደረገ መ/ቤት ላይ እርምጃ ስለመወሰዱ፡-

44. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

45. ኤጀንሲው በሚያደርገው የሂሳብ ምርመራ በርካታ ያልተሰበሰበ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ሂሳብ መኖሩ እየታወቀ በተለይ በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ የልማት ድርጅቶች በርካቶቹ ወደ ግል ይዞታ ሲዛወሩ ሊከፍሉት የሚገባቸው ውዝፍ የጡረታ መዋጮ እዳ ያለባቸው ሆኖ ይህንን ውዝፍ ሂሳብ ገቢ ለማድረግ በኤጀንሲው በኩል ለህግ ክፍል ተላልፈው የህግ እርምጃ እንዲወሰድባቸው አለመደረጉ ታውቋል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ከህግ ክፍል ከቀረበው ማስረጃ ለመረዳት እንደተቻለው ከ2002 እስከ 2004 ድረስ የህግ ጉዳዮች ዳይሬክተር

ክትትል ተደርጎባቸው ክስ ከመሰረተባቸው 44 ክሶች ውስጥ ውዝፍ የጡረታ ሂሳብን በተመለከተ የተከሰሱት 6 (ስድስት) መ/ቤቶች ብቻ ሲሆኑ፣ የተቀሩት በግለሰቦች ላይ የተመሰረተ ተመላሽ የአበል ክፍያን የሚመለከት ክስ መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

46. ያልተሰበሰበ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ሂሳብ እንዲሰበሰብ ለማድረግ ግዴታቸውን ባልተወጡ የጡረታ መዋጮ ከፋዮች እና ሰብሳቢ አካላት ላይ የህግ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

47. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሐጣት.1/16/94/05 በቀን 12/07/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር እስከ መጋቢት 30/2006 ዓ.ም ውዝፍ ያለባቸውን መ/ቤቶች በመለየት ከድጎማ በጀታቸው ላይ ተቀንሶ ለኤጀንሲው ገቢ እንዲደረግ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እንደሚያሳውቅ ገልጿል፡፡

48. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

49. የመንግስት ሠራተኞች የጡረታ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 907/2007 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የሚፈለግበትን የጡረታ መዋጮ በ 30 ቀን ውስጥ ገቢ ያላደረገ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም በራሱ ገቢ የሚተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤት ገቢ ባልተደረገው የጡረታ መዋጮ ላይ ደመወዝ ከተከፈለበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ በባንክ ማስቀመጫ ወለድ መጠን መሠረት ከሚታሰብ መለድ እና አምስት በመቶ (፭%) ቅጣት ጨምሮ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

50. ሆኖም የጡረታ መዋጮ የመንግስትና የሠራተኛውን ድርሻ ቀንሰው በወቅቱ ለፈንዱ ገቢ ሳያደርጉ የቀሩ የመንግስት መ/ቤቶች ላይ የሚወሰድ እርምጃን በተመለከተ የጡረታ መዋጮ ገቢ ምርመራ በማድረግ ልዩነቶች ከተገኙ በአስቸኳይ እንዲያስገቡ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ በመፃፍ ፣በማስጠንቀቂያው መሠረት በተሰጠው ጊዜ ገደብ ካላስገቡ በመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ ማሻሻያ አዋጅ መሠረት ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ተጨማሪ ክፍያና የባንክ ወለድ ጨምሮ በማሰብ ከባንክ አካውንታቸው እንዲቀነስ የማድረግ ሥራ እንደሚሰራ፣ ባለበጀት መ/ቤቶች ከወጪ መርጃ እየተቀነሰ ገቢ እንዲሆን እንደሚደረግ የኤጀንሲው የምዝገባና አበል ውሳኔ ዳይሬክቶሬት የስራ ሃላፊ በቀረበላቸው ቃለ-መጠየቅ ገልፀዋል፡፡

51. የኤጀንሲው የምዝገባና አበል ውሳኔ ዳይሬክቶሬት የስራ ሃላፊ ይህን ይበሉ እንጂ በመሀል ሪጅን ፅ/ቤት ከሠራተኞች ሊቀነስ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በመቀነስ በወቅቱ

ለፈንዱ ገቢ ያላደረገ የመንግስት መ/ቤቶች ላይ እንዲከፍሉ የተለያዩ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤዎችን ከመፃፍ ውጪ እርምጃ እንደማይወስዱ፣

52. በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ከሠራተኛ ሊቀነስ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ ቀንሰው ለጡረታ ፈንዱ በወቅቱ ለፈንዱ ገቢ ሳያደርጉ የቀሩ የመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች ከሆነ ከበጀታቸው እንዲቀነስ የሚደረግ ሲሆን ፣ በራሳቸው በጀት የሚተዳደሩ የመንግስት መ/ቤቶች ከሆኑ ደግሞ ከባንክ ሒሳባቸው ላይ እንዲቀነስ የሚደረግ መሆኑን፣

53. በአርባምንጭ ቅ/ፅ/ቤት ከመንግስት መ/ቤቶች የተሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ያላደረጉ መ/ቤቶች ክፍያውን እንዲፈፅሙ ከማድረግ ውጪ ምንም ዓይነት ቅጣት እንደማይቀጡ ፣

54. በሶዶ ቅ/ፅ/ቤት ከሠራተኞች ደሞዝ ሊቀነስ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ ቀንሰው በወቅቱ ለፈንዱ ገቢ ሳያደርጉ የቀሩ የመንግስት መ/ቤቶች የተወሰደባቸው እርምጃ የሌለ መሆኑን፣ ለምሳሌ :- በሶዶ ቅ/ፅ/ቤት ውስጥ ከሚገኙ አሰሪ መ/ቤቶች መካከል በ2008 በጀት ዓመት በወላይታ ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት የሲቪል ሠራተኛ 98,790.01 /ዘጠና ስምንት ሺ ሰባት መቶ ዘጠና ብር ከ ዜሮ አንድ ሳንቲም/ ፣ ከወታደር 142,601.88 /አንድ መቶ አርባ ሁለት ሺ ስድስት መቶ አንድ ብር ከ ሰማንያ ስምንት ሳንቲም/ በድምሩ ብር 241,391.89 /ሁለት መቶ አርባ አንድ ሺ ሶስት መቶ ዘጠና አንድ ብር ከሰማንያ ዘጠኝ ሳንቲም ያልተከፈለ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ እዳ ያለበት መሆኑን፣

55. በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት ከሠራተኞች ሊቀነስ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ ቀንሰው በወቅቱ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ሳያደርጉ የቀሩ የመንግስት መ/ቤቶች ከበጀታቸው ወይም ከአካውንታቸው እንዲቀነስ ከማድረግ ውጪ የሚወሰድባቸው እርምጃ የሌለ መሆኑን፣

56. የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ያለበት ሲሆን ይህንን ውዝፍ ለማስከፈል ከአካውንታቸው ላይ እንዲቀነስ በተደጋጋሚ ለሆሳዕና ቅርንጫፍ ንግድ ባንክ በደብዳቤ ቢያሳውቁም ባንኩ ፈቃደኛ አለመሆኑን፣ የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች በተደረገላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

57. እንዲሁም የክትትል ኦዲት ቡድኑ በናሙና ተመርጠው ከታዩ የሪጅን ፅ/ቤት እና ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች የምርመራ ሪፖርት ለመመልከት እንደቻለው ከሠራተኞች ሊቀነስ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በመቀነስ በወቅቱ ለፈንዱ ገቢ ያላደረጉ መ/ቤቶች ውዝፍ

የጡረታ መዋጮውን ከማስከፈል ውጪ በአዋጁ መሰረት ምንም ዓይነት ቅጣት እንዲቀጡ እና ወለዱን እንዲከፍሉ የማይደረግ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

58. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ገቢ በማያደርጉ ባለበጀት አሰሪ የመንግስት መ/ቤቶች በወቅቱ የጡረታ መዋጮ ገቢ ካልሆነ እዳው ከሚሰጣቸው በጀት ድጎማና የወጪ መርጃ ላይ በመቀነስ ገቢ የሚደረግ ሲሆን በራሳቸው በጀት የሚተዳደሩና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ያለባቸውን ውዝፍ የጡረታ መዋጮ በአዋጁ ድንጋጌ መሠረት የባንክ ወለድና 5% ቅጣት ተጨምሮ እንዲከፍሉ እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

59. ይሁን እንጂ በኤጀንሲው በማስረጃነት የቀረበው ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ያለባቸው የመንግስት የልማት ድርጅቶች በኤጀንሲው ዋናው መ/ቤት ስር ብቻ ያሉ አሰሪ መ/ቤቶች ሲሆኑ የሪጅን ፅ/ቤት እና ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች በማስረጃው ያልተካተቱ መሆናቸው፣ የባንክ ወለድና 5% ቅጣት ተጨምሮ እንዲከፍሉ ስለመደረጉ ደግሞ የባንክ ስቴትመንት ባለመቅረቡ ማስረጃው ተቀባይነት የለውም፡፡

ለጡረታ ፈንዱ የሚያገለግለውን የሂሳብ አሰራር ማንዋል (መመሪያ) ወቅታዊ /ዘመናዊ/ እንዲሆን ስለመደረጉ፡-

60. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

61. የኤጀንሲውን የጡረታ ፈንድ የሚመለከቱ አዋጆች እና ደንቦች በየጊዜው ተሻሽለው በመውጣት አሰራሩም እንደዚሁ በአዲስ መልክ እየተለወጠ ሲሆን፣ ለጡረታ ፈንዱ ሂሳብ አያያዝ የሚያገለግለው ማንዋል (መመሪያ) በ1992 ዓ.ም የተዘጋጀና ከ13 ዓመት በላይ የቆየና በጥናቱ መሰረት እንዲሻሻል ያልተደረገ መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

62. ለፈንዱ ሂሳብ አያያዝ የሚያገለግለው የሂሳብ አሰራር ማንዋል (መመሪያ) ወቅታዊ ሊደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

63. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሐጣት.1/16/94/05 በቀን 12/07/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ እስከ ሰኔ 30/2007 ዓ.ም የሂሳብ አሰራር ማኑዋሎችን ወቅታዊ እንደሚያደርግ ገልጿል ።

64. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

65. በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ለጡረታ ፈንዱ የሚያገለግል በ1992 ዓ.ም የወጣ መመሪያ እና ቻርት እንዳለ እና መመሪያውን ወቅታዊ /ዘመናዊ / ለማድረግ የተሰራ ስራ የሌለ መሆኑን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

የጡረታ ፈንድ አቋም የሚያሳይ የሂሳብ ትንታኔ (የሂሳብ መግለጫ) በየዓመቱ መዘጋጀቱን እና ኦዲት መደረጉን በተመለከተ፡-

66. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

67. በፋይናንስና አስተዳደር አዋጅ መሰረት የበጀት አመቱ ባለቀ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ሂሳባቸውን መዝጋት ሲገባቸው የ2003 እና 2004 ሂሳብ ያልተዘጋ መሆኑ፤ የጡረታ ፈንድ አቋም የሚያሳይ የሂሳብ ትንታኔ ያለመዘጋጀቱ እንደዚሁም የጡረታ ፈንዱ ሂሳብ ከ2002 በኋላ ኦዲት ያልተደረገ መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

68. የ 2003 እና የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብን በመዝጋት የጡረታ ፈንዱን ሂሳብ የሚያሳይ የሂሳብ መግለጫ ሊዘጋጅና ሂሳቡም ኦዲት ሊደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

69. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሐጣት.1/16/94/05 በቀን 12/07/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ እስከ ግንቦት 30/2005ዓ.ም የ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስደርጎ ማጠናቀቅ ፣እና እስከ ሰኔ 30/2005 ዓ.ም የ 2004 በጀት ዓመት ሂሳብ መዝጋት እና ለኦዲተር አቅርቦ እንደሚያስመረምር ገልጿል።

70. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

71. በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የ2006 ዓ.ም እና የ2007 ዓ.ም የሂሳብ መግለጫ የተዘጋጀ ሲሆን ፣ የ2008 ዓ.ም የሂሳብ መግለጫ ያላለቀ መሆኑን ፣ የኦዲት ሪፖርትን በተመለከተ ደግሞ የ2006 ዓ.ም ብቻ ያለ ሲሆን የ2007 ዓ.ም ኦዲት ስራው በኦዲት ኮርፖሬሽን እየተሰራ መሆኑን፣ በ 2008 ዓ.ም ኦዲት እንዳልተደረገ ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

72. እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩ የኤጀንሲው ሪጅን ፅ/ቤቶች እና ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች የሒሳብ አካውንት የሌላቸው በመሆኑና ከአሰሪ የመንግስት መ/ቤቶች የሚሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ ገቢ እንዲደረግ የሚያደርጉት በዋናው መ/ቤት በተከፈተ

የጡረታ ፈንድ አካውንት ስለሆነ የሒሳብ ትንታኔ/ የሒሳብ መግለጫ/ የማያዘጋጁ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በአሰሪ መ/ቤቶች ስም የተከፈተው የገቢ ሂሳብ ሌጀር ወቅታዊ ስለመሆኑ፡-

73. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

74. በናሙና ለኦዲት ቡድኑ የቀረቡት ሌጀሮች ሲከለሱ ምዝገባው በአብዛኛው ሚያዚያ 2003 ላይ የተቋረጠ መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

75. የጡረታ መዋጮ ገቢ ሂሳብ በአሰሪ መ/ቤቶች ሥም በተከፈተ ሌጀር ተመዝግቦ እንዲያዝ ሊደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

76. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሐጣት.1/16/94/05 በቀን 12/07/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ እስከ ሰኔ 30/2005 ዓ.ም የሌጀር ምዝገባ ወቅታዊ እንደሚደረግ ገልጿል ።

77. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

78. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የኤጀንሲው የሪጅን ፅ/ቤቶች እና ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች መካከል በመሀል ሪጅን ፅ/ቤት በአዲስ አበባ ሪጅን ፅ/ቤት ፣ በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ፣ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሂሳብ በአሰሪ መ/ቤቶች ሥም በተከፈተ ሌጀር ተመዝግቦ እንዲያዝ የተደረገ ሲሆን ፣ በአርባምንጭ ቅ/ፅ/ቤት የ2006 ዓ.ም እና የ2007 ዓ.ም ሌጀር ፖስት የተደረገ ሲሆን የ 2008 ዓ.ም ፖስት ያልተደረገ /ያልተመዘገበ/ መሆኑን፣ በወላይታ ሶዶ ቅ/ፅ/ቤት ከ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሂሳብ በአሰሪ መ/ቤቶች ሥም በተከፈተ ሌጀር ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑን ፣ በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት በአሰሪ መ/ቤቶች ስም የተከፈተ የ 2006 ዓ.ም ሌጀር የሌለ ሲሆን የ2007 እና የ 2008 ዓ.ም ደግሞ በተሟላ መልኩ ፖስት ያልተደረገ /ያልተመዘገበ/ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

79. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ በዋናው መ/ቤት፣ በሪጅኖችና በአብዛኛው በቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች የገቢ ሂሳብ ሌጀር ምዝገባ ክፍተቶችን ወስደው የማስተካከል እና ወቅታዊ የማድረግ ስራ እንደሚከናወን ገልፀዋል፡፡

ለሪል ስቴት ወጪ ተደርጎ የተከፈለው ሂሳብ የተመለሰ ስለመሆኑ እና ቦታው ለሚመለከተው የመንግስት አካል መረከቡን በተመለከተ፡-

80. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

81. ኤጀንሲው ለተለያዩ አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉ ህንጻዎች ለመገንባት አሰላ፤ ደሴ፤ ጅማ እና ደብረማርቆስ ለሚካሄድ ሪል ስቴት ብር 5,301,741.17 ወጪ ተደርጎ ከተከፈለ በኋላ መንግሥት የኤጀንሲውን ኢንቨስትመንት በተመለከተ አዲስ አቅጣጫ በማስቀመጡ ከተጀመረው የሪል ስቴት ልማት እንዲወጣ የተደረገ መሆኑ፣

82. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በዚሁ ውሳኔ መሰረት ቀደም ሲል በሊዝ ኤጀንሲው የተረከበውን ቦታ ለማስረከብና ውሉ እንዲቋረጥ የተከፈሉ የተለያዩ ወጪዎችም ተመላሽ እንዲሆኑ በ17/09/03 ለጅማ ከንቲባ ጽ/ቤት፤ በ20/11/2003 ለአሰላ ከተማ ከንቲባ ጽ/ቤት፤ በ9/09/2003 ለደሴ ከተማ አገልግሎት እና በ10/09/2003 ለደብረማርቆስ ከተማ ከንቲባ ከተጻፈ ደብዳቤ ውጭ ለሪልስቴቱ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲሆን የተደረገ ክትትል አለመኖሩ እና ደብረማርቆስ እና አሰላ ከተማ የሚገኘውን ቦታ ለከተሞቹ ማዘጋጃ ቤቶች ለማስረከባቸው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

83. ለፈንዱ ኢንቨስትመንት አያያዝና አጠቃቀም የቁጥጥር እና የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት በተዘረጋው ስርአት መሰረት ለሪል ስቴቱ ወጪ የተደረገው ገንዘብ ለወደፊቱ እንዲሰበሰብ በማድረግ የሂሳብ ምዝገባውም ከኢንቨስትመንት ወደ ተሰብሳቢ ዞሮ እንዲመዘገብና ኤጀንሲው ቦታውን ያስረከበበት ማስረጃም ሊቀርብ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

84. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሐጣት.1/16/94/05 በቀን 12/07/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ እስከ ሰኔ 30/2005 ዓ.ም የተለፈለውን ገንዘብ በአስተዳደራዊ መንገድ እንዲመለስ ክትትሉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ፣ እስከ ሚያዚያ 30/2005 ዓ.ም ለአሰላ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ቦታውን ለማስረከባችን ማስረጃ እንደሚያቀርብ ገልጿል ።

85. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

86. ኤጀንሲው ለተለያዩ አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉ ህንጻዎች ለመገንባት አሰላ፤ ደሴ፤ ጅማ እና ደብረማርቆ ለሚካሄድ ሪል ስቴት ብር 5,301,741.17 ያወጣ ሲሆን ከእነዚህ መካከል የደሴ ከተማ ብር 84,496 / ሰማንያ አራት ሺ አራት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ገቢ የተደረገ መሆኑን ፣ የጅማ ብር 355,548.46 ገቢ የተደረገ ሲሆን የአሰላ እና የደብረማርቆስ ጉዳዩ በህግ የተያዘ መሆኑን ስራው ከሚመለከታቸው የሥራ ሀላፊዎች ቃለ-መጠይቅ እና ከማስረጃዎች ታውቋል፡፡

87. ኤጀንሲው ለተለያዩ አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉ ህንጻዎች ለመገንባት ለሪል ስቴቱ ከደብረማርቆስ እና ከአሰላ ተረክቦ የነበረውን ቦታ ለሚመለከተው የመንግስት አካል እንዲረከብ የተደረገ መሆኑን የደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ፅ/ቤት በቀን 12/12/2005 በቁጥር ከን-4323/በ-10 እንዲሁም የአሰላ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በቀን 2/11/2005 በቁጥር - Mq/7494/m.35/05 ለመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ በፃፈው ደብዳቤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የገንዘብ መክፈያ ፔይሮል ላይ በጣት አሻራ ብቻ በተደረገ ምልክት ሂሳብ ስለመወራረዱ፡-

88. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

89. የጡረታ አበል ክፍያ የሚፈጸመው ኤጀንሲው በሚወክላቸው ከፋይ ተቋማት (ፖስታ አገልግሎት ድርጅት፤ ኮሜርሻል ኖሚነስ፤ ብድርና ቁጠባ ተቋም፤) ሲሆኑ ከፋይ ተቋማቱም ክፍያ በሚፈጽሙበት ጊዜ ባለመብቱ ይዞት በሚቀርበው የመክፈያ ካርድ ላይ ምልክት በማድረግና ባለመብቱንም በመክፍያ ሰነድ (ፔሮል) ላይ በአብዛኛውን የጡረታ ባለመብት በጣት አሻራ ፊርማ ብቻ በማስፈረም ሲሆን ሂሳቡም የሚወራረደው በዚሁ በጣት አሻራ በተፈረመ የመክፈያ ሰነድ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህንንም ክፍያ ለትክክለኛ ባለመብቱ የተከፈለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኤጀንሲው በአመት አንድ ጊዜ የጡረተኞች ቆጠራ የሚያደርግ ሲሆን ከዚህ ውጭ አበላቸውን ሳይወስዱ እንደወሰዱ ተደርጎ ሂሳቡ በጣት አሻራ በተፈረመ የመክፈያ ሰነድ ከተወራረደ በኋላ ባለመብቶቹ ያልተፈረመበትን የክፍያ ካርድ በመያዝ ወደ ኤጀንሲው ሲመጡ አበሉ እንዲከፈላቸው የሚደረግ መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

90. የጡረታ አበል ለትክክለኛው ባለመብት መከፈሉ በኤጀንሲው ሊረጋገጥ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

91. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሐጣት.1/16/94/05 በቀን 12/07/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ ከላከው የድርጊት መርሃ ግብር መካከል የገንዘብ መክፈያ ፔይሮል ላይ በጣት አሻራ ብቻ በተደረገ ምልክት ሂሳብ መወራረዱን በተመለከተ በመርሃ -ግብሩ ላይ አላካተተም፡፡

92. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

93. መፈረም ከሚችሉ የጡረታ ባለመብቶች መካከል አብዛኛው በጣት አሻራ እንዲፈርሙ የሚደረግ መሆኑን ፣ ይህም የሆነበት ምክንያት በእርጅና ምክንያት በሚፈርሙበት ጊዜ ስለሚንቀጠቀጡ ያለቦታው ስለሚፈርሙ ፣ በእርጅና ምክንያት የማየት ችግር ስላለባቸው ፣ ክፍያውን ለማፋጠን እና ክፍያ አልተፈፀመልኝም የሚል ግለሰብ ካለ በአሻራ ምርመራ በቀላሉ ለመለየት ስለሚቻል እንደሆነ እና ለትክክለኛ ባለመብት ስለመከፈሉ የሚረጋገጠው የጡረታ ባለመብቶች ከኤጀንሲው ይዘው በሚመጡት ካርድ ወይም ውክልና ያላቸው ደግሞ ህጋዊ ውክልና ይዘው ሲመጡ መሆኑን ከሪጅን ፅ/ቤቶች ፣ ከቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች እና ከጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

94. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ጡረተኞች በፅሁፍ ፊርማ እንዲፈርሙ በማድረግ የጡረታ አበሉን እንደሚወስዱ፣ በእርጅና፣በህመም እና በሌሎች ተዛማች ችግሮች የተነሳ መፈረም የማይችሉትን ጡረተኞችን ደግሞ በጣት አሻራ እየፈረሙ ክፍያው እንዲፈፀምላቸው የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

95. ኤጀንሲው ይህን ይበል እንጂ መፈረም ከሚችሉ የጡረታ ባለመብቶች መካከል አብዛኛው በጣት አሻራ እንዲፈርሙ የሚደረግ መሆኑን በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከከፋይ ተቋማት ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ እንዲሁም ከክፍያ ፔሮሎች ታውቋል፡፡ በመሆኑም የተሰጠውን አስተያየት ለመቀበል አልተቻለም፡፡

የጡረታ ፈንዱ የማስረጃ አያያዝና አጠባበቅ አንድ ወጥ እና አስተማማኝ መሆኑን በተመለከተ ፡-

96. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

97. የመንግሥት ሠራተኞች የምዝገባ መረጃም በሁለት አይነት መንገድ መያዙ በኮምፒዩተር መስራት በሚችሉ የኤጀንሲው ሰራተኞች በሶፍት ኮፒ ሲያዝ ኮምፒዩተር መጠቀም በማይችሉት ሰራተኞች ደግሞ በማንዋል (በእጅ) እየተመዘገበ እንዲያዝ መደረጉን ፣

98. ስለጉዳዩ በናሙና የተመረጡ አሰሪ መ/ቤቶች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ማስረጃዎች የተሟሉ ባለመሆናቸው ባለመብቶች መብታቸውን በተገቢው ጊዜ ሳይጉላሉ እንዲያገኙ አለመደረጉን እና የማስረጃ አያያዝም ላይ ክፍተት በመኖሩ መብታቸውን

ለማስከበር የሚጠይቁ ባለጉዳዮች እንደገና እንደ አዲስ ማስረጃ እንዲያመጡ ስለሚደረግ ባለጉዳዩ በመመላለስ እየተጉላላ መታየቱን ተገኝቶ ነበር፡፡

99. የመንግሥት ሠራተኛ የምዝገባ ማስረጃና የጡረታ ፈንዱን የሚመለከቱ ማሰረጃዎች በአግባቡና አስተማማኝ በሆነ የመረጃ አያያዝ ዘዴ ሊጠበቅ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

100. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሐጣት.1/16/94/05 በቀን 12/07/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ እስከ ሰኔ 30/2005 ዓ.ም የምዝገባ መረጃን ወጥ በሆነ መልኩ በኮምፒውተር \pension admin system\ እንዲመዘገብ እንደሚያደርግ ገልጿል።

101. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

102. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የኤጀንሲው የሪጅን እና የቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች መካከል በመሀል ሪጅን ፅ/ቤት ፣ በአዲስ አበባ ሪጅን ፅ/ቤት እና በዋናው መ/ቤት የመንግሥት ሠራተኞችን ምዝገባ የሚመለከቱ ማስረጃዎች የመረጃ አያያዝ በባህር መዝገብ /በማንዋል/ እና በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ /በፔንሽን አድሚን ሶፍትዌር/ እንደሆነ የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ ቢገልፁም በፔንሽን አድሚን ሶፍትዌሩ ላይ መረጃዎች ሙሉ ለሙሉ እየተመዘገቡ አለመሆናቸውን የክትትል ኦዲት ቡድኑ ለመመልከት ችሏል፡፡

103. እንዲሁም በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ፣ በአርባምንጭ ቅ/ፅ/ቤት ፣ በሶዶ ቅ/ፅ/ቤት እና በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት የመንግሥት ሠራተኞችን ምዝገባ የሚመለከቱ ማስረጃዎች የመረጃ አያያዝ በባህር መዝገብ /በማንዋል/ እና በሶፍት ኮፒ / በወርድ ወይም በኤክሴል / ሲሆን ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ / ፔንሽን አድሚን ሶፍትዌር / የሌላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

104. በተጨማሪም ኤጀንሲው የጡረታ ፈንዱን የሚመለከቱ ማስረጃዎች ደግሞ በማንዋል የተያዙ መሆኑን ፣ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ እንደሌላቸው ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ታውቋል፡፡

የቋሚ የመንግስት ሠራተኞች የምዝገባ ማስረጃ ተሟልቶ እንዲቀርብ እና የማህበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር በወቅቱ እንዲሰጥ ስለመደረጉ

105. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

106. በናሙና ከታዩት ሪጅን ጽ/ቤቶች ውስጥ ከ1990 እስከ 2001 ድረስ ለተቀጠሩ ሰራተኞች መለያ ቁጥር እንዲሰጣቸው ከዋናው መ/ቤት መለያ ቁጥሩ ተልኮ ፋይሉን እያደራጁ መሆኑን፤ በናሙና ከታዩት አሰሪ መ/ቤቶችም ከቀረበው ቃለ መጠይቅ ለመረዳት እንደተቻለው፤ ሰራተኞች የጡረታ ጊዜያቸው ሲደርስ እየተቸገሩ መሆኑን እና መ/ቤቶች እራሳቸው የሰራተኞቻቸውን መረጃ አሟልተው የማይልኩ መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

107. አሰሪ መ/ቤቶች የቋሚ ሠራተኞችን የምዝገባ ማስረጃ አሟልተው እንዲልኩ ሊደረግ እና የመንግሥት ሠራተኛ የምዝገባ ማስረጃ ተሟልቶ ሲቀርብ የማኅበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር በወቅቱ ሊሰጠው እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

108. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሐጣት.1/16/94/05 በቀን 12/07/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ ከላከው የድርጊት መርሃ ግብር መካከል ለመንግስት ሰራተኞች የማህበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር በወቅቱ እንዲሰጥ ስለማድረግ በመርሃ -ግብሩ ላይ አላካተተም፡፡

109. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

110. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የምዝገባ ማስረጃ ተሟልቶ ሲቀርብ የማኅበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር በወቅቱ እንደሚሰጠው ከመሀል ሪጅን ፅ/ቤት፣ ከደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ፣ ከአዲስ አበባ ሪጅን ፅ/ቤት ፣ ከአርባምንጭ ቅ/ፅ/ቤት ፣ ከሶዶ ቅ/ፅ/ቤት እና ከሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ ቀርቦላቸው በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

111. ኤጀንሲው ለግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ሠራተኞች የማህበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር በወቅቱ የማይሰጣቸው መሆኑን፣ በመ/ቤታቸው 23 ሠራተኞች ያሉ ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል የጡረታ መለያ ቁጥር ያለው አንድ ግለሰብ ብቻ ሲሆን እርሱም ከዚህ ቀደም ሲሰራ ከነበረበት የመንግስት መ/ቤት ይዞ የመጣው መሆኑን፣ እንዲሁም ኤጀንሲው ለወላይታ ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት ሠራተኞች የጡረታ መለያ ቁጥር በወቅቱ እንደማይሰጣቸው እና የመለያ ቁጥር ለማግኘት ብዙ እንደሚመላለሱ ከስራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

112. እንዲሁም የአርባምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ከመንግስት ወደ ግል ድርጅት የተቀየረ ሲሆን በመንግስት መ/ቤት ስር እያለ ይሰሩ የነበሩ እድሜያቸው ለጡረታ የደረሱ ሰራተኞች የጡረታ አበል በግል ድርጅት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ሊወሰንላቸው ማህደራቸው ከመንግስት ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ሲጠየቅ ወደ ስምንት የሚሆኑ ሰራተኞች ፋይል የጠፋ ሲሆን አበል ለመወሰን የተቸገሩ መሆኑን ከግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ እና ከኤጀንሲው ጋር ከተፃፃፉቸው ደብዳቤዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለጡረታ መዋጮ ሰብሳቢዎች ፣ አበል ከፋዮች እና አሰሪ መ/ቤቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ስለመዘጋጀቱ ፡-

113. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

114. ሥራው ለሚመለከታቸው ሰራተኞች (ለጡረታ መዋጮ ሰብሳቢዎች ስለሚሰበስቡት የጡረታ መዋጮ አሰባሰብና ማስረጃ አያያዝና አላላክ፤ ለጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት የጡረታ አበል ክፍያ ለትክክለኛው ባለመብት ስለመክፈል፤ ለአሰሪ መ/ቤቶች የሰራተኛውን ህይወት ታሪክ ማስረጃ አስሞልቶ በወቅቱ ስለመላክ፤ በአዋጅ ቁጥር 714/2033 መሰረት ስለሚቆረጠው የጡረታ መዋጮን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ አለመሰጠቱን ተገኝቶ ነበር፡፡

115. ኤጀንሲው ለጡረታ መዋጮ ሰብሳቢዎች እና አበል ከፋይ ተቋማት እንደዚሁም ለአሰሪ መ/ቤቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ሊያዘጋጅ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

116. ኤጀንሲው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሐጣት.1/16/94/05 በቀን 12/07/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ ከላከው የድርጊት መርሃ ግብር መካከል ለጡረታ መዋጮ ሰብሳቢዎች እና ለጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ተዘጋጅቶ ስለሚሰጥ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ በመርሃ -ግብሩ ላይ አላካተተም፡፡

117. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

118. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ መ/ቤቶች መካከል ከመሀል ሪጅን ፅ/ቤት፣ ከደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ፣ ከአዲስ አበባ ሪጅን ፅ/ቤት ፣ ከአርባምንጭ ቅ/ፅ/ቤት፣ ከሶዶ ቅ/ፅ/ቤት ፣ እና ከሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት የስራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለጡረታ

መዋጮ ሰበሳቢዎች እና ከፋይ ተቋማት በየዓመቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ተዘጋጅቶ እንደሚሰጣቸው ገልፀዋል፡፡

119. ኤጀንሲው ይህን ይበል እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የጡረታ ከፋይ እና ሰብሳቢ አካላት ለመረዳት እንደተቻለው ኤጀንሲው ለደ/ብ/ብ/ክ/መ/ ገቢዎች ባለስልጣን፣ ለደቡብ ሪጅን ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ፣ ለአርባምንጭ ከተማ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት፣ ለአርባምንጭ ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ፣ ለአርባምንጭ ከተማ ገቢዎች ባለስልጣን፣ ለወላይታ ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ፣ ለሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ዋና ፅ/ቤት እና ለኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ሆሳዕና ቅርንጫፍ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ አዘጋጅቶ ሰጥቷቸው የማያውቅ ሲሆን፣ ለወላይታ ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት እና ለወላይታ ዞን ገቢዎች ባለስልጣን ደግሞ ከ 2006 እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ አንድ ጊዜ ብቻ የግንዛቤ ማስጨበጫ የተሰጣቸው መሆኑን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

120. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ የኤጀንሲው መ/ቤትም ሆነ ሪጅን ፅ/ቤቶች ለአሰሪ የመንግስት መ/ቤቶች በጡረታ አዋጅ እና አፈፃፀም ዙሪያ በየጊዜው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ እንደሚያከናውኑ ገልፀዋል፡፡

121. ኤጀንሲው ይህን ይበል እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የጡረታ ከፋይ እና ሰብሳቢ አካላት መካከል ለደ/ብ/ብ/ክ/መ/ ገቢዎች ባለስልጣን፣ ለደቡብ ሪጅን ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ፣ ለአርባምንጭ ከተማ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት፣ ለአርባምንጭ ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ፣ ለአርባምንጭ ከተማ ገቢዎች ባለስልጣን፣ ለወላይታ ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ፣ ለሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ዋና ፅ/ቤት እና ለኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ሆሳዕና ቅርንጫፍ ኤጀንሲው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ አዘጋጅቶ ሰጥቷቸው የማያውቅ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም የተሰጠውን አስተያየት ለመቀበል አልተቻለም፡፡

ክፍል ሦስት

የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)

122. በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የጡረታ ፈንድ አሰባሰብ ፣ አያያዝ እና አጠቃቀም በተመለከተ ተከናወኖ በቀረበው የኦዲት የማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎችና እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- በባለበጀት መ/ቤቶች የጡረታ መዋጮ ሰብሳቢዎች ላይ በዓመት አንድ ጊዜ አሰሪ መ/ቤቶች በመሄድ ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑ፤
- ለጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ላይ ደግሞ ለጡረታ ባለመብቶች ክፍያ ከተፈፀመ በኋል በክፍያ በክፍያ ፔሮሉ መሰረት ትክክለኛነቱን በማረጋገጥና መተማመኛ በመፈራረም ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ፣
- ከባለበጀት መ/ቤቶች የሚሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ከየትኞቹ መ/ቤቶች እንደተሰበሰበ የሚታወቅ መሆኑን፣
- ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ያለባቸው መ/ቤቶች ላይ በኤጀንሲው በዓመት አንድ ጊዜ ምርመራ የሚደረግ መሆኑ፡-
- የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ለፈንዱ ገቢ ሳያደርጉ የቀሩ የመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች ላይ የጡረታ መዋጮ ገቢ ምርመራ በማድረግ ልዩነቶች ከተገኙ በአስቸኳይ እንዲያስገቡ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ የሚፃፍ መሆኑ ፣ ከባንክ አካውንታቸው እንዲቀነስ የሚደረግ መሆኑን ፣ ከባለበጀት መ/ቤቶች ከወጪ መርጃ እየተቀነሰ ገቢ እንዲሆን እንደሚደረግ፣
- በኤጀንሲው ዋና መ/ቤት፣ በመሀል ሪጅን ፅ/ቤት እና በአዲስ አበባ ሪጅን ፅ/ቤት የመንግሥት ሠራተኞችን ምዝገባ የሚመለከቱ ማስረጃዎች የመረጃ አያያዝ በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ / በፔንሽን አድሚን ሶፍትዌር / መሆኑ፣

መኖሩ ታውቋል፡፡

3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው

- በራሳቸው በጀት የሚተዳደሩ መ/ቤቶች የጡረታ መዋጮ የሚሰበሰበው በገቢዎች ባለስልጣን ሲሆን በገቢዎች ባለስልጣን ላይ በራሳቸው በጀት ከሚተዳደሩ መ/ቤቶች የጡረታ መዋጮ በትክክል ስለመሰብሰቡ ቁጥጥር እና ክትትል የማይደረግ መሆኑን፣
- ከሠራተኞች የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ በወቅቱ ገቢ የማይደረግበት መሆኑን ፣ በገቢዎች ባለስልጣን የሚሰበሰበው በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ መ/ቤቶች የጡረታ መዋጮ ከየትኞቹ መ/ቤቶች እንደተሰበሰበ በአብዛኛው የማይታወቁ መሆኑን፣
- ከሠራተኞች ሊቀነስ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በመቀነስ በወቅቱ ለፈንዱ ገቢ ያላደረገ የመንግስት የልማት መ/ቤቶች ላይ ወለድ እና አምስት ፐርሰንት ቅጣት እንዲከፍሉ የማይደረግ መሆኑን፣
- ለጡረታ ፈንዱ የሚያገለግል በ1992 ዓ.ም የወጣ መመሪያ ወቅታዊ / ዘመናዊ / ለማድረግ የተሰራ ስራ የሌለ መሆኑን፣
- የጡረታ ፈንድ አቋም የሚያሳይ የሂሳብ ትንታኔ (የሂሳብ መግለጫ) በየዓመቱ እየተዘጋጀ እና ኦዲት እየተደረገ አለመሆኑ፣
- አንዳንድ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች የጡረታ መዋጮውን በአሰሪ መ/ቤቶች ሥም በተከፈተ ሌጀር መዝግበው ያልያዙ መሆኑን ፣
- ኤጀንሲው ለተለያዩ አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉ ህንጻዎች ለመገንባት ካወጣው 5,301,741.17 ብር ውስጥ የአሰላ እና የደብረማርቆስ ገቢ ያልተደረገ መሆኑን ፣
- መፈረም ከሚችሉ የጡረታ ባለመብቶች መካከል አብዛኛው በጣት አሻራ እንዲፈርሙ የሚደረግ መሆኑን፣
- የመንግሥት ሠራተኞችን ምዝገባ የሚመለከቱ ማስረጃዎችን በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ / ፔንሽን አድሚን ሶፍትዌር / ያላቸው ሪጅን ፅ/ቤቶች በተሟላ ሁኔታ ያልተመዘገበ መሆኑን ፣ በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ / ፔንሽን አድሚን ሶፍትዌር / የሌላቸው ሪጅን እና ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች መኖራቸው፣

- የጡረታ ፈንዱን የሚመለከቱ ማስረጃዎች ደግሞ በማንዋል የተያዙ ሲሆን ፣ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ የሌለ መሆኑን ፣
- የቋሚ የመንግስት ሠራተኞች የምዝገባ ማስረጃ ተሟልቶ እንዲቀርብ እና የማህበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር በወቅቱ እንዲሰጥ የማይደረግ መሆኑ፣
- ለጡረታ አበል ከፋይ እና ሰብሳቢ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ተዘጋጅቶ የማይሰጣቸው መሆኑን፣

  እስካሁን መኖሩ ታውቋል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)

123. በመጀመሪያው የክዋኔ ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች የተወሰኑት የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው፡፡

124. ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ባልተስተካከሉና የእርምት እርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት አስፈለጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በክትትል ኦዲት ወቅት የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና በናሙና የታዩት የጡረታ አበል ሰበሳቢ ፣ ከፋይ እና አሰሪ መስሪያቤቶች ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1

በመህል ሪጅን ፅ/ቤት ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ያለባቸው መቤቶች

ተራ ቁ	የመ/ቤቱ ስም	ምርመራ የተደረገበት የበጀት ዓመት								ውዝፍ ዕዳ ድምር
		2006		2007		2008		2009		
		ውዝፍ ዕዳ	የገባ	ውዝፍ ዕዳ	የገባ	ውዝፍ ዕዳ	የገባ	ውዝፍ	የገባ	
1.	ኢሉ ገላን ገ/ኢ/ል/ጽ/ቤት	-		1,709.04	-	-				1,709.04
2.	አጃጅ ከተማ አስተዳደር	-			-	113,139.15				113,139.15
3.	ባላም ከተማ አስተዳደር	-			-	2,997.13	797.71			2,199.13
4.	ባኬ ከተማ አስተዳደር	-			-	6,585.61	-			6,585.61
5.	ጉቴ ከተማ አስተዳደር	-			-	7,128.36	-			7,128.36
6.	አምቦ ከተማ ውሃናፍሳሽ	-		502,238.36	502,238.36	2,000.00	-			2,000.00
7.	አምቦ ማዘጋጃ ቤት	-	-	-	-	165,698.00				165,698.00
8.	ሸኖ ከተማ አስተዳደር			27,203.88	-	-	-			27,203.88
9.	ቀጥቀጦ ከተማ አስተዳደር			12,244.00	-	2,280.10	-			14,524.10
10.	ሙገር			39.88	-	-	-			39.88
11.	ባቢች ከተማ አስተዳደር	-	-	--	-	1,130.54				1,130.54
12.	ጌዶ ውሃና ፍሳሽ	-	-	-	-	163.93	-			163.93
13.	ጌዶ ከተማ አስተዳደር	-	-	-	-	86,341.30	-			86,341.30
14.	አዳበር ውሃና ፍሳሽ	-	-	-	-	28,055.50				28,055.50
15.	ባኮትቤ ገ/ኢ/ል/ ጽ/ቤት			18.00	18.00	291,493.00				291,493.00
16.	ጀልዱ ገ/ኢ/ል/ ጽ/ቤት			17,657.32		48,417.70				66,075.02
17.	ጮቢ ከተማ አስተዳደር			36,529..50		-				36,529..50
18.	ጎጆ የከተማ አስተዳደር			10,501.80	-	30,398.24				40,900.04
19.	ጎጆ የከተማ ውሃና ፍሳሽ					120.24				120.24
20.	ግንደበረት ገ/ኢ/ል/ጽ/ቤት	-	-	-	-	55511.10				55511.10
21.	ጨሉጤ ከተማ አስተዳደር	-	-	-	-	15,317.50				15,317.50
22.	ኤጀሬ ውሃና ፍሳሽ	-	-	-	-	52.50				52.50
23.	ቦዳ ከተማ አስተዳደር					5,873.85				5,873.85
24.	ጊንጪ ከተማ አስተዳደር			8,286.05	-	-	-			8,286.05
25.	ባኬ ቀላጤ ከተማ አስተዳደር					2,815.81				2,815.81
26.	ቆርኬ ማዘጋጃ ቤት	1,045.76	-	9,894.24	-	-	-			9,894.24
27.	ገርቦ ማዘጋጃ ቤት	522.88	-	60,333.06	-	-	-			60,855.94
28.	ጪቱ ማዘጋጃ ቤት	1,437.36	-	15,782.42--		312..90				17532.68
29.	ሀሮ ወንጪ ማዘጋጀ ቤት /ከ2004 እስከ 2008 መጋቢት /	3,267.04	-	0.12		2, 591.64	-			5858.68
30.	ጊንዶ ማዘጋጃ ቤት	-	-	-	-	551.12	-			551.12
31.	ቡሳ መጠጥና ውሃ አገልግሎት	1523.68	-	744.14	-	-	-			2199.14
32.	ሀርቡ ጬልሌ ማዘጋጃ ቤት	-	-	51995.48	-					51,995.48

ተራ ቁ	የመ/ቤቱ ስም	ምርመራ የተደረገበት የበጀት ዓመት								ውዝፍ ዕዳ ድምር
		2006		2007		2008		2009		
		ውዝፍ ዕዳ	የገባ	ውዝፍ ዕዳ	የገባ	ውዝፍ ዕዳ	የገባ	ውዝፍ	የገባ	
33.	ሀጭበር ጨፌ ማዘጋጃ ቤት	2.678.24	-	.	13203.18	-	-			15,881.00
34.	ኢሉ ገ/ኢ/ል/ጽ/ቤት	33,996.23	-		18,389.45	18,389.45				33,996.23
	ጠ/ድምር									**1,141,28.04**
	በሆሳዕና ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ያለባቸው መቤቶች									
35.	የስልጤ ዞን ፋ/ኢ/ል/ መምሪያ ዞን ማዕከል ፋይናንስ	-	-	1,331,399.34	-	-	-			1,331,399.34
36.	የስልጤ ዞን ኢንዱስትሪያል ኮሌጅ	-	-	51,408.52						51,408.52
37.	የስልጤ ዞን ማዕከል	-	-	332,918.01						332,918.01
38.	ወራቤ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ	-	-	96,491.25						96,491.25
39.	ወራቤ ከተማ አስተዳደር	-	-	240,866.17						240,866.17
40.	ሁልባረግ ወረዳ ፋ/ኢ/ል	*	-	777,109.40						777,109.40
41.	ሁልባረግ ወረዳ ኬራቴ ከተማ ማዘጋጃ ቤት	-	-	41,854.48						41,854.48
42.	ላንፍሮ ወረዳ ፋ/ኢ/ል/ፅ/ቤት		-	557,734.08						557,734.08
43.	የስለጤ ዞን ላንፍሮ ወረዳ ፖሊስ	-	-	44,196.09						44,196.09
44.	የላንፍሮ ወረዳ ጦራ ከተማ ማዘጋጃ ቤት	-	-	59,068.44						59,068.44
45.	የላንፍሮ ወረዳ ሚቶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት	-	-	31,212						31,212
46.	ዳሎች ወረዳ ፋ/ኢ/ል/ፅ/ቤት		-	772,707.83						772,707.83
47.	ዳሎችወረዳፖሊስ	-	-	309,017.56						309,017.56
48.	የዳሎችወረዳ ከተማ ማዘጋጃ ቤት		-	51,889.46						51,889.46
49.	ምስ/አዘርነትበ/ወ/ፋ/ኢ/ል/ ጽ/ቤትፖሊስ	-	-	242,097.44						242,097.44
50.	ቁለጦ ከተማ ማዘጋጃ ቤት		-	16,601.28						16,601.28
51.	ምዕ/አዘርነትበ/ወ/ፋ/ኢ/ል/ ጽ/ቤትፋይናሰ	-	-	493,337.80						493,337.80
52.	ምዕ/አዘርነትበ/ወ/ፋ/ኢ/ል/ ጽ/ቤትፖሊስ	-	-	230,421.70						230,421.70
53.	ቦኖሽ ከተማ ውሃ	-	-	39,005.30						39,005.30
54.	ደንሌም ፎንቅ ታዳጊ ማዘጋጃ	-	-	53,516.16						53,516.16

ተራ ቁ	የመ/ቤቱ ስም	ምርመራ የተደረገበት የበጀት ዓመት								ውዝፍ ዕዳ ድምር
		2006		2007		2008		2009		
		ውዝፍ ዕዳ	የገባ	ውዝፍ ዕዳ	የገባ	ውዝፍ ዕዳ	የገባ	ውዝፍ	የገባ	
55.	ሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ፋ/ኢ/	-	-	9,268,861.86						9,268,861.86
56.	አንጋጫ ወረዳ ማዘጋጃ ቤት	-	-	55,093.26						55,093.26
57.	ከምባታ ጠምባሮ ዞን አንጋጫ ወረዳ ፋ/ኢ/ል ወታደር	-	-	51,204.68		51,204.68				51,204.68
58.	ዶዮገና ወረዳ ማዘጋጃ ቤት	-	-	90,567.87						90,567.87
59.	ዶዮገና ወረዳ ወሃ /አገ/ ድርጅት	-	-	266,61.76						266,61.76
60.	ዶዮገና ወረዳ አመቾዋቶ ማ/ቤት	-	-	3,764.88						3,764.88
61.	ኩተሌ ከተማ ማዘጋጃ ቤት	-	-	11,656.44						11,656.44
62.	ያቃቁቶ ከተማ ታዳጊ ማዘጋጃ ቤት	-	-	22,015.08						22,015.08
63.	ስልጤ ወረዳ ቅቤት ከተማ አገልግሎት	-	-	3,127.74						3,127.74
64.	ስልጤ ወረዳ አልኮል ከተማ ማዘጋጃ ቤት	-	-	1,431.36						1,431.36
65.	ስልጤ ወረዳ ኡደላ ከተማ ማዘጋጃ ቤት	-	-	2,459.63						2,459.63
66.	ስልጤ ወረዳ ኤሎስ ከተማ አገልግሎት	-	-	963.18						963.18
67.	ስልጤ ወረዳ ቅባት ማዘጋጃ ቤት	-	-	12,403.73						12,403.73
68.	ስልጤ ወረዳ ፖሊስ	-	-	404,759						404,759
69.	ስልጤ ወረዳ ፋ/ኢ/ል	-	-	893,860.77						893,860.77
70.	ጠ/ድምር									**16,176,897.25**
የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አጀንሲ ዋናው መ/ቤት ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ያለባቸው										
71.	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	-	-	181,390.55						181,390.55
72.	የሀገር ጥበብ ማደራጃ ድርጅት	-	-	560.40						560.40
73.	የትምህርት መሣሪያቻች ማምረቻ ድርጅት	-	-	27,574.62						27,574.62
74.	የአንበሳ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት	-	-	40,441.94						40,441.94
75.	የመድሃኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ መረጃ ያልተገኘ	-	-	128,455.79						128,455.79
76.	በኢትዩጵያ የኢንዱስትሪ ግብአቶች ልማት ድርጅት	-	-	683.88						683.88
77.	የስኳር ኮርፖሬሽን	-	-	55115.38						55115.38
78.	ትራንስፖርትና ኮንስትራክሽን ዲዛይን	-	-	155,708						155,708

ተራ ቁ	የመ/ቤቱ ስም	ምርመራ የተደረገበት የበጀት ዓመት								ውዝፍ ዕዳ ድምር
		2006		2007		2008		2009		
		ውዝፍ ዕዳ	የገባ	ውዝፍ ዕዳ	የገባ	ውዝፍ ዕዳ	የገባ	ውዝፍ	የገባ	
	ሼር ካምፓኒ									
79.	ኢትዮጵያ ልማት ባንክ	-	-	-	-	-	-	18377.7		18377.7
80.	ኢትዮጵያ ፕረሰ					147418.7	-			147,418.7
81.	ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፋይናንስ ሥራ አስፈፃሚ ጽ/ቤት							3,731,807.27		3,731,807.27
82.	ኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ዘርፍ					4,327.68				4,327.68
83.	ትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት					631..02				631..02
84.	ብረታ ብረት ኢንጅነሪግ ኮርፖሬሽን የሀይ-ቴክ ኢንጅነሪግ ኢንዱሰትሪ					922.65				922.65
85.	ብረታ ብረት ኢንጅነሪግ ኮርፖሬሽን የኢትዮጵያ ፓወር ኢንጅነሪግ ኮርፖራሽን					1,438.67				1,438.67
86.	ብረታ ብረት ኢንጅነሪግ ኮርፖሬሽን የሎጀስቲክ ሳፕላይ					667.58				667.58
	በአርባ ምንጭ ቅ/ፅ/ቤት ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ያለባቸው መቤቶች									
87.	የዲታ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት የሲቪል 135,083.40 እና የወታደር 100,573.76 ተደምሮ	-	-	-	-	235,657.16				235,657.16
88.	የጋሞ ጎፋ ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ የ2008 ዓ.ም የሲቪል ሠራተኞች የ2009	-	-	-	-	2,226,483.15	-	7,302.08	-	2,233,785.23
89.	የአርባምንጭ ከተማ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት የሲቪል ሠራተኞች ብር 6,101,753.57 እና የወታደር ብር 947,393.52 በድምሩ	-	-	-	-	7,049,147.09				7,049,147.09
	ጠቅላላ ድምር									**9,518,589.92**

ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ያለባቸው እና በ 2009 በፍ/ቤት ክትትል የሚደረግባቸው መ/ቤቶች

	የመ/ቤቱ ሥም	ክርክር የሚደረገበት የገንዘብ መጠን								
90.	ለሙ ከምከም ወረዳ ገ/ኢ/ል/ፅ/ቤት	5,303,412.17								
91.	ምስራቅ በለሳ ወረዳ ገ/ኢ/ል/ፅ/ቤት	753,117.49								
92.	ዙሀሙሲት መሪ ማዘጋጃ ቤት	95,725.27								
93.	ምዕራብ ዕስቴ ገ/ኢ/ል/ፅ/ቤት	988,435.4								
94.	ዕብናት ወረዳ ገ/ኢ/ል/ፅ/ቤት	641,152.30								
95.	ደቡብ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት	3,807,280.77								
96.	ሀርቀሎ ከተማ አስተዳደር	107,936.27								
97.	አርባ ሙዳ ከተማ ማዘጋጃ ቤት	162,933.68								
	ጠ/ድምር									11,859,993.4